## የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ብሔራዊ ምክር ቤት (ሽንጎ) ሦስተኛው አስቸኳይ ጉባዔ ውሳኔዎች

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሀገሪቱን አንድነትና ህልውና ጠብቆ፥ ከአምባገነን አገዛዝ ተላቆ፥ እኩልነትንና ፍትሕን አስፍኖ በደስታና በሰላም ለመኖር ካለው ጽኑ ፍላጎት የተነሳ ለረዥም ጊዜ ታግሏል። በግንቦት 97 ዓ.ም. ምርጫ ሚሊዮኖች ወደ ምርጫ ጣቢያዎች የሄዱትና ድምፃቸውን የሰጡት የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ካላቸው ፍላጎት የተነሳ ነው። ይህ የሕዝባችን ቁርጠኛ አቋም በአሸባሪው አምባገኑ የሕወሐት/ ኢሕአዴግ የማን አለብኝና ግፈኛ አገዛዘ ተጨናግፎ፥ ሕዝባችን የጨለማ፥ የስቃይና የችግር ኑሮ እንዲቀጥል ተገድዷል። ጨቋኝና አፋኝ የሆኑት የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች በርካታ ወገኖቻችንን በአደባባይ በመረሸን፥ በብዙ ሺ የሚቆጠሩትን በማጎሪያ ጣቢያዎች በማሠር፥ በሺዎች ላይ ሰቆቃዊ ድርጊት በመፈጸም፥ የፖለቲካ ድርጅቶችንና የሲቪክ ማኅበራትን በማፍረስና መሪዎቻቸውንና አባሎቻቸውን አስረው በማሰቃየት የሕዝባችንን ትግል ለማፈን ሞክረዋል። በዚህም የለየላቸው አሸባሪ አምባገነኖች መሆናቸው አረጋግጠዋል።

ከምርጫው ወዲህ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለው ስቃይና መከራ በብዙ እጥፍ ተበራክቶና ተስፋፍቶ ሕዝባችን መኖር በማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ከምርጫው በፊት በከባድ ትግል ተገኝተው የነበሩት የዴሞክራሲ ጭላንጭል መብቶች ሙሉ በሙሉ ተዘግተው ዛሬ መብትን ለመጠየቅም ሆነ ተደራጅቶ ለመንቀሳቀስ ወይም በነፃ ሀሳብን ለማስፋፋት የማይቻልበት ብቻ ሳይሆን የማይሞከርበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

የተያዘው የለየለት ቅልበሳ እንደ መሆኑ መጠን የአገራችን ዴሞክራቶች ይህንን የጥፋት ሂደት በጋራ ትግል ተረባርበው እስካላቆሙት ድረስ ይህ የአፈና ውርጂብኝ በሽብር በተዋከበና በአመራር ክፍተት ግራ በተጋባ ኅብረተሰብ ውስጥ እንደሚቀጥል አጠያያቂ አይደለም። በአግራጭ ፕሮግራማችን ያጋለጥናቸው አጥፊ የአኮኖሚና ማኅበራዊ ፖሊሲዎች ቀጥለው በርሃብ- በመናጢ ድህነት በጅምላ ስራ አጥነት- በአካባቢ ውድመት ሆነ በሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች አገራችን የማትወጣው የቀውሶች አዙሪት ውስጥ እንደምትገባም መጠራጠር አይቻልም።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ አምባገነን አገዛዝ ሽብርተኛነትን በመዋጋት ስም የባዕድ አገሮችን ተልእኮ ለማሟላት በሶማሊያ ላይ የፈጸመው ጣልቃ ገብነትና እንዲሁም በአገሪቱ ውስጥ በልዩ ልዩ ቦታዎች ሽብርተኛነትን በመዋጋት ሰበብ የውጭ ዜጎች የሚታሠሩበትና ሰቆቃዊ ድርጊት የሚፈጸምባቸው እስር ቤቶች ማቋቋሙ ለአሁኑ ትውልድ ብቻ ሳይሆን ለተከታታይ ትውልዶች የሚተላለፍ ጠንቅ እየጋበዘ መሆኑ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ገሃድ የወጣ እውነታ ነው። ሕወሓት/ኢሕአዴግ የሰማሊያን የሽግግር መንግሥት ለመርዳት በሚል ምክንያት ወታደሮችን ወደ ሶማሊያ በመላክ ከእስላማውያኑ ኃይሎች ጋር ያደረገው ጦርነት የሕዝባችንን ደህንነት ወይም ሀገርን ከውጭ ጠላት ለመከላከል የተደረገ እርምጃ ሳይሆን የውጭ ኃይሎችን ፍላጎት ለማሟላትና የአገዛዙን እድሜ ለማራዘም የሚያስችል ድጋፍና ርዳታ በማግኘት አፈናውን ለማባባስ


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
ስልክ/Tel. 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

5. ከግንቦቱ ምርጫ ወዲህ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች የወሰዱትን የድምፅ ስረቃና የሽብር እርምጃዎች በመቃወም አንዳንድ የምዕራብ አገሮች በአሸባሪው አገዛዝ ላይ የወሰዱት የማዕቀብ እርምጃ በወጭ እርዳታ እስትንፋስ አግኝቶ ይንቀሰቃስ የነበረውን አሸባሪ ቡድን ያስደነገጠ ለሕዝባችን ተስፋ የሰጠ እርምጃ በመሆኑ ኅብረቱ አድናቆቱን ገልጿል፡፡ ከጥቂት ጊዜ ወዲህ የዓለም አቀፉን የሽብር ጦርነት ለመቋቋም ረዳት ይሆነናል በሚል አንዳንድ አገሮች በተለይም አሜሪካ ለአሸባሪው የኢሕአዴግ አገዛዝ የሚሰጡት የገንዘብ፥ የመሣሪያና የሞራል ድጋፍ በሽብር ተግባሮቹ እንዲሰማራ ይበልጥ የሚያበረታቱት መሆናቸውን ኅብረቱ እየገለጸ የሕዝብ መብት ገድቦ በሀገሪቱ ዜጎች ላይ የሽብር ተግባሮችን የሚያካሂድ መንግሥት ዓለም አቀፍ ሽብርን ለመቋቋም ይረዳናል ብሎ ማሰብ ትርጉም የለሽ ከመሆኑም በላይ የሽብር ተግባርን የሚያጠናክር፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለባሰ ስቃይና በደል የሚዳርግ እርምጃ መሆኑን ኅብረቱ በጥብቅ ያስገነዝባል፡፡ መንግሥታት ለአሸባሪው አገዛዝ እየሰጡ ያለውን ድጋፍና ትብብር እንዲያቋርጡ እየጠየቅን ሕዝባችን ለዴሞክራሲ የሚያደረገውን ትግል በመደገፍ ትብብር እንዲያደርጉ ጥሪ እናደርጋለን፡፡

በመጨረሻም በሀገር ውስጥና በመላው ዓለም የተቋቋሙት የኅብረቱ የድጋፍ አካላት ኅብረቱ እያካሄደ ያለውን ትግል በመደገፍና ትግሉን ለማጠናከር ላበረከቱት ጉልህ አስተዋጽኦ ኅብረቱ አድናቆቱን ገልጾ ይበልጥ ውስብስና ጠመዝማዛ የሆነው ሕዝባዊ ትግል ተጠናክሮ እንዲቀጥል አሁንም ድጋፋቸውና ሁለገብ ተሳትፏቸው እንዲቀጥል ኅብረቱ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡ ተወካዮቻቸውንም በመላክ ላደረጉትም አስተዋጽኦ ምስጋናውን ይገልጻል፡፡

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት
ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ)

ሚያዚያ 2 ቀን 1999 ዓ.ም.